Buusaa Gonofaa

Microfinance S.C./ *W.A. Maayikroofaayinaansii*

ቡሳ ጎኖፋ

ማይክሮፋይናንስ (አ.ማ.)

# የባለአክሲዮኖች 11ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣ 367(1)፣ እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 16(1) መሠረት የቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሰኔ 20 ቀን 2018 ዓ.ም. ከጧቱ 2፡30 ሰዓት ጀምሮ በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

1. **ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች፣**
   1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ፣አ.አ. ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 312፣ ዌብ ሳይት www.bgmfi.com ኢ-ሜይል info@bgmfi.com ፖስታ ሣ. ቁጥር 24850 ኮድ 1000፣ ስልክ ቁጥር +251-114-16-26-21፣
   1.2. የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፣-KK/AA/3/0001649/2004፣
   1.3. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፣ 75,000,000፣
   1.4. የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፣ 75,000,000፣
2. **የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች**
   **2.1. የጉባኤውን አጀንዳዎች ማጽደቅ፣**
   **2.2. የአክሲዮን ማህበሩን ካፒታል ማሳደግ፣**
   **2.3. የአክሲዮን ማህበሩን የመመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 10 ማሻሻል፣**
   **2.4. የጠቅላላ ጉባኤውን ቃለ-ጉባኤ መስማት እና ማጽደቅ፣**
3. **ማሳሰቢያ፣**
   3.1. በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ሥልጣን ባለው የመንግሥትአካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በ**ቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር ዋና መሥሪያ ቤት** በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ በመሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡
   3.2. የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤ ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ብጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

**የቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር ዳይሬክተሮች ቦርድ**